አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ሁለቱም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ህግ ቁጥር 337 መሰረት ይግባኙን በትዕዛዝ ዘግተዋል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ጉዳይ ላይ ነው፡፡ አመልካች ሰኔ 10/2014 ዓ.ም አሻሽሎ ባቀረበው አራት ገፅ የሰበር አቤቱታ በስር የአስተዳደር አካላት ውሳኔ እና በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶቹ ትዕዛዝ ላይ ተፈፅሟል ያለውን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሶ በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ ፍሬ ሀሳቡም በ2008 ዓ.ም በጀት ዓመት አመልካች አ/ማ ያገኘው የተጣራ ትርፍ ለባለአክሲዮኖች ሳይከፋፈል ለካፒታል ማሳደጊያነት እንዲውል ህዳር 10/2009 ዓ.ም በተካሄደው የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ተወስኗል፤ በዚሁ ውሳኔ መሰረት በበጀት አመቱ የተገኘው የተጣራ ትርፍ ብር 48,993,500.55(አርባ ስምንት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሶስት ሺህ አምስት መቶ ብር ከ55/100) ለድርጅቱ ካፒታል ማሳደጊያነት እንዲውል ተደርጎ የድርጅቱ ካፒታል በዚሁ መጠን አድጓል፤ ይህ ለመሆኑም ውሳኔው የፀደቀበት ቃለ ጉባኤ በሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ተመዝግቦ በህጉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ማስረጃው ለተጠሪ ተሰጥቷል፤ ለካፒታል ማሳደጊያነት የዋለ ትርፍ ላይ ግብር የማይከፈል ስለመሆኑ የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር በ1996፣ 2005 እና 2011 ያወጣቸው መመሪያዎች የሚደነግጉ መሆኑን፤ አመልካች ያገኘውን ትርፍ ለካፒታል ማሰደጊያነት አውሎ እያለ አስቀድሞ ላደገ ካፒታል መክፈያ የዋለ በመሆኑ ለእዳ መክፈያነት እንጂ ለካፒታል ማሳደጊያነት የዋለ ነው ሊባል አይቻለም በሚል ምክንያት ግብር እንዲከፍል መወሰኑ የመመሪያዎቹ መሰረታዊ ዓላማ ያላገናዘበ መሆኑን፤ ካፒታል በምን መልኩ ማደረግ እንዳለበት የመወሰኑ ድርሻ የኩባንያዎች እና አግባብነት ያለው የንግድ ህግ በመሆኑ ቀድሞ ቃል ለተገባ እና ላልተከፈለ የአክሲዮን እዳ መክፈያነት የዋለ ትርፍ ከኩባንያው ወጥቶ ለባለአክሲዮኖች እስካልተከፈለ ድረስ ለካፒታል ማሳደጊያነት አልዋለም ሊባል አይችልም፤ ይህ ጉዳይ በዚህ ችሎት በክርክር ላይ እያለ ተጠሪ መ/ቤት በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ አስቀድሞ ለተፈረመ እና ቃል ለተገባ የአክሲዮን ግገር የተከፈለ የተጣራ ትርፍ ለካፒታል ማሳደጊያነት አልዋለም ሊባል አይችልም በሚል ሌሎች ግብር ከፋዮችን ከግብር ነፃ አድርጓል፤ የሰበር አቤቱታውን ማሻሻል ያስፈለገውም በዚሁ ምክንያት መሆኑን በመግለፅ በተጣራው ትርፍ ላይ ግብር እንዲከፈል በተጠሪ ተወስኖ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፀናው ውሳኔ ተሽሮ አመልካች ከግብር ነፃ ነው ሊባል ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በ2008 በጀት አመት ያገኘውን የተጣራ ትርፍ ለካፒታል ማሳደጊያነት አላዋለም በሚል ምክንያት በተገኘው ትርፍ ላይ ግብር እንዲከፍል የተወሰነበት አግባብ በዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመታዘዙ ተጠሪ የፅሁፍ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

በዚሁ አግባብ ተጠሪ ሐምሌ 24/2014 ዓ.ም የተፃፈ 7 ገፅ መልስ አቅርቧል፡፡ መሰረታዊ ይዘቱም በኩባንያ የበጀት ዓመት የተጣራ ትርፍ ላይ ስለሚጣል የገቢ ግብርን አስመልክቶ በወጡት መመሪያዎችም ሆነ ሰርኩላሮች መሰረት የተጣራ ትርፍ ከግብር ነፃ የሚሆነው ለድርጅቱ ካፒታል ማሳደጊያነት የዋለ ስለመሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፤ የአመልካች ካፒታል ከነበረበት ብር 1,220,000(አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሃያ ሺህ ብር) ወደ ብር 439,540,000(አራት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሚሊዮን አምስት መቶ አርባ ሺህ ብር) ያደገው መጋቢት 29/2004 ዓ.ም ሲሆን በ2005 ዓ.ም

እና ከዚህ ጊዜ በኋላ የታደሰው የአመልካች የንግድ ፈቃድም ይህንኑ የሚያሰዩ መሆኑን፤ አመልካች በ2008 ዓ.ም በጀት ዓመት ያገኘው የተጣራ ትርፍ በእርግጥም ለካፒታል ማሳደጊያነት የዋለ ቢሆን ኖሮ የድርጅቱ ካፒታል ከዚህ በላይ ማሳየት የሚጠበቅበት ሲሆን ከዚህ አኳያ አመልካች ያቀረበው ማስረጃ የለም፤ ህዳር 10/2009 ዓ.ም ተደረገ የተባለው መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤም የተጣራው ትርፍ ለካፒታል ማሳደጊያነት ይዋል የሚል አይደለም፤ ይልቁንም ቀደም ሲል የኩባንያው ካፒታል እንዲያድግ በተላለፈው ውሳኔ መሰረት የተፈረመውን አክሲዮን ከፍለው ላልጨረሱት ባለአክሲዮኖች የአክሲዮን ግዢ እዳ እንዲውል፤ ከፍለው ለጨረሱት ደግሞ ትርፉ እንዲሰጣቸው የሚል ነው፤ በዚሁ አግባብ የተጣራው ትርፍ ቀድሞ ቃል ለተገባ እና ለተገዛ የአክሲዮን ድርሻ እዳ ማካካሻነት የዋለ እንጂ የአመልካች ኩባንያን ካፒታል ያላሳደገ በመሆኑ ለካፒታል ማሳደጊያነት ውሏል ሊባል አይችልም፤ ቀድሞ ለተፈረመ የአክሲዮን ድርሻ እዳ ክፍያ የዋለ ትርፍ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 2/10/፣ 34 እና 60 መሰረት ለባለአክሲዮኑ እንደ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም/ገቢ/ የሚቆጠር በመሆኑ ግብር ሊከፈልበት የሚገባ ነው፤ ተጠሪ መስሪያ ቤትም ሆነ በየደረጃው ያሉት የዳኝነት አካላት በትርፉ ላይ ግብር እንዲከፈል የወሰኑትም ይህንኑ ተገንዝበው በመሆኑ ውሳኔው ተገቢ ነው፤ በተመሳሳይ ጉዳይ ሌሎች ግብር ከፋዮች ከግብር ነፃ ተደርገዋል በሚል የቀረበው ቅሬታ በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ያልቀረበ በመሆኑ በዚህ ደረጃ ሊቀርብ አይገባም፤ ተሰጠ የተባለው ውሳኔም ቢሆን የህዝብ እና የመንግስት ጥቅምን በእጅጉ የሚጎዳ መሆኑ ተረጋግጦ አዋጁ በሚፈቅደው መሰረት ስህተቱ እንዲታረም ለክቡር ሚኒስቴሩ ቀርቦ በመታየት ላይ በመሆኑ ፍፃሜ ያገኘ ጉዳይ አይደለም፤ ጽ/ቤቱም ቢሆን የሚሰጠው ውሳኔ እንደየትኛውም የበታች ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚታይ በመሆኑ ችሎቱን የሚያስገድደው ባለመሆኑ የቀረበው የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ ውሳኔው ሊፀና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና መሰረታዊ የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገበዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ዋናው የክርክር ምክንያት ከመታየቱ በፊት ጉዳዩ በዚህ ችሎት በመታየት ላይ እያለ ከክርክሩ ጭብጥ ጋር በተያያዘ የገንዘብ ሚኒስቴር ሰርኩላር አውጥቷል በሚል ይህንኑ አስመልክቱ በግራ ቀኙ ክርክር የቀረበ በመሆኑ በዚሁ ነጥብ ላይ አንድ ነገር ማለቱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

አመልካች መስከረም 06/2015 ዓ.ም ባቀረበው አቤቱታ በዚህ ችሎት በመታየት ላይ ካለው ክርክር ጋር በተያያዘ የገንዘብ ሚኒስቴር ነሐሴ 11/2014 ዓ.ም የአመልካችን መከራከሪያ የሚደግፍ ሰርኩላር ያወጣ መሆኑን ጠቅሶ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ሲሰጥ የተጠቀሰውን ሰርኩላት ከግንዛቤ እንዲያስገባለት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ በዚሁ አቤቱታ ላይ መከራከሪያ ካለው እንዲያቀርብ በታዘዘው መሰረት ተጠሪ ታህሳስ 11/2015 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ሰርኩላር ተብሎ የቀረበው ማስረጃ የፌዴራል አስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 የሚጥስ ነው የሚልበትን ምክንያት በመዘርዘር እንዲሁም

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

CamScanner

ሚኒስትሩ ከስልጣን ውጭ ያወጡት በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም የሚልበትን ምክንያት ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡

ይኸው ጉዳይ በምርመራ ላይ እንዳለ የአሁን ተጠሪ የካቲት 27/2015 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ አመልካች "የገንዘብ ሚኒስትር ያወጣው ሰርኩላር ነው" በማለት ያቀረበውን ደብዳቤ አስመልክቶ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ ውጤትን የሚያስከትሉ መልዕክት የያዙ ህጋዊ ሰነዶችን በሰርኩላር መልክ ማውጣት ከፌዴራል አስተዳደር ስነ ስርዓት አዋጁ ጋር የሚጋጭ መሆኑን ጠቅሶ መሰል ሰነዶች ካሉ በአዋጁ በተመለከተው አግባብ የመመሪያ አወጣጥ ስርዓትን በተከተለ መልኩ እንዲፈፀም ለተጠሪ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች በደብዳቤ ያሳወቀ መሆኑን በመግለፅ ቀደም ሲል በአመልካች የቀረበውን ሰነድ አስምልክቶ ካቀረበው መከራከሪያ አንፃር ይኸው በምርመራ ወቅት እንዲታይለት ጠይቋል፡፡ ገርሃ

አመልካች በዚሁ አቤቱታ ላይ መጋቢት 13/2015 ዓ.ም ባቀረበው መልስ የተጠሪ አቤቱታ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም የሚልባቸውን መከራከሪያዎች ጠቅሶ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡

ችሎቱም በግራ ቀኙ የቀረቡትን አቤቱታዎች እና አንዱ በሌላኛው አቤቱታ ላይ ያቀረቧቸውን መከራከሪያዎች መርምሯል፡፡ በዚሁ መሰረት አመልካች ገንዘብ ሚኒስቴር ያወጣው ሰርኩላር ነው በማለት ከአቤቱታው ጋር ያቀረበው ሰነድ ለአሁን ተጠሪ መ/ቤት በቀጥታ የተፃፈ ደብዳቤ መሆኑን ከሚገልፅ በቀር አመልካች በገለፀው አኳኋን ሰርኩላር መሆኑን የሚገዕልፅ ነገር የለውም፡፡ የደብዳቤው ይዘት ሲታይም ለባለአክሲዮኖች ያልተከፋፈለ የንግድ ድርጅት ትርፍን አስመልክቶ በፌዴራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀፅ 61 ስር የተመለከተው ድንጋጌ ሊተረጎም የሚገባበትን አኳኋን የሚገልፅ ነው፡፡

በሌላ በኩል የፌዴራል አስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 ስራ ከዋለበት መጋቢት 29/2012 ጀምሮ መመሪያን የማውጣት ስልጣን በተሰጣቸው በማናቸውም አስተዳደር አካላት የሚወጣው መመሪያ በአዋጁ አንቀፅ 7-10 ስር በተመለከተው አግባብ መውጣት ያለበት መሆኑን በአዋጁ አንቀፅ 4/2/ ስር ተመልክቷል፡፡ በአዋጁ መሰረት መመሪያ የሚባለውም በህግ አውጪ አካል በሚሰጠው የውክልና ስልጣን መሰረት በአስተዳደር ተቋም የሚወጣ እና በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ ውጤት የሚያስከትል የህግ ሰነድ ሲሆን በስራ ላይ ያለ መመሪያን የሚያሻሽል ወይም የሚሽር የህግ ሰነድንም የሚጨምር ስለመሆኑ በአንቀፅ 2/2/ ስር ተመልክቷል፡፡ በቅርጽ ደረጃም የሚወጣው መመሪያ የመመሪያውን ተራ ቁጥር፤ መመሪያው እንዲወጣ የስልጣን ምንጭ የሆነውን ህግ፤ የመመሪያውን አጭር ርዕስ፤ ትርጓሜ፣ የተፈፃሚነት ወሰን፣ ዋና ዋና ድንጋጌዎች፤ የማሻሻያ፣ መሻሪያ፣ መሸጋገሪያ፣ ማቆያ ድንጋጌ ካለ ይህንኑ የሚመለከት ድንጋጌ፤ እንዲሁም መመሪያው የወጣበትና ተፈፃሚ የሚሆንበትን ቀን የያዘ መሆን እንደሚገባው በአዋጁ አንቀፅ 15 ስር ተመልክቷል፡፡

ከዚህ አንፃር አመልካች ያቀረበው ሰነድ የፌዴራል አስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጁ ስራ ላይ ከዋለ በኋላ የተፃፈ ሲሆን በይዘትም ሆነ በቅርጽ ደረጃ ሲታይ በተቋም ደረጃ የተፃፈ ደብዳቤ ነው ከሚባል በቀር የመመሪያ መልክም ሆነ መመሪያን ለማስፈፀም የወጣ አስገዳጅነት ያለው ዝርዝር ህግ መልክ ያለው አይደለም፡፡ በመሆኑም የቀረበው ሰነድ በአዋጁ በተመለከተው አግባብ ያልወጣ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ

[signature] 27-7-2015

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

የመ.ቁ.214263

መጋቢት 27/2015 ዓ.ም

---

ከዚህ የመመሪያው ዝርዝር ይዘት በግልፅ መረዳት እንደሚቻለው በአንድ የግብር ዘመን የተገኘ የድርጅት የተጣራ ትርፍ ከግብር ነፃ የሚሆነው የተገኘው ትርፍ ለባለአክሲዮኖቹ ሳይከፋፈል ለኩባኒያው ካፒታል ማሳደጊያነት የዋል እንደሆነ እና የኩባንያው የካፒታል መጠንም በበጀት ዓመት በተገኘው ትርፍ ልክ ያደገ ስለመሆኑ በመመሪያው በተመለከተው የማስረጃ ዓይነት ማረጋገጥ የተቻለ እንደሆን ብቻ ነው፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካች በ2008 ዓ.ም የበጀት ዓመት ያገኘውን የተጣራ ትርፍ ለካፒታል ማሳደጊያነት አውየዋለሁ የሚለው ትርፉን ለባለአክሲዮኖች ሳይከፋፈል የአክሲዮን ድርሻ ክፍያ እዳቸውን ላልጨረሱት ባለአክሲዮኖች እዳ ክፍያነት ያዋልኩ በመሆኑ ይኸው የካፒታል እድገት ተብሎ ሊያዝ ይገባል በማለት ነው፡፡ ከዚህ ውጭ በመመሪያው በተመለከተው መሰረት በበጀት አመቱ በተገኘው የተጣራ ትርፍ ልክ የድርጅቱ ካፒታል ማደጉን የሚያሳይ ማስረጃ አቅርቢያለሁ የሚል ክርክር የለም፡፡ በሌላ በኩል የአመልካች ድርጅት ካፒታል በ2004 ዓ.ም ካደገ በኋላ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ አዲስ የካፒታል እድገት ድርጅቱ በየዓመቱ በሚያቀርበው የታደሰ የንግድ ፈቃድ ላይ የማይስተዋል ስለመሆኑ ተጠሪ ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡ አመልካች ይህንን በመካድ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በ2008 ዓ.ም የተገኘውን የተጣራ ትርፍ በ2004 ዓ.ም የድርጅቱ ካፒታል ሲያድግ ባለአክሲዮኖች ቃል ለገቡት የአክሲዮን ድርሻ እድገት እዳ ማካካሻነት መዋሉ የተገኘው ትርፍ ለካፒታል እድገት ውሏል የሚያስብ ባለመሆኑ አመልካች ከዚህ አኳያ የሚያቀርበው ክርክር የህግ መሰረት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም አመልካች በ2008 በጀት ዓመት ባገኘው የተጣራ ትርፍ ላይ ግብር እንዲከፍል በተጠሪ መወሰኑ እና በየደረጃው ያሉት መደበኛ ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ በመቃበላቸው የፈፀሙት መሰረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ የአመልካች መከራከሪያ ውድቅ ተደርጎ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ**

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/202864 ላይ ሰኔ 23/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠው የመጨረሻ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

**ትዕዛዝ**

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም